# አስቾኳይ ጥሪ ለወገን

## - የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ዋዜማና የጥቁር ሕዝብ ትንሳኤ

ከየሺወርቅ ወንድሜነህ

አሌፖ ላይ የሚወርደው ቦምብ አልቆመም። የሶሪያዊቷ እናት ልጆቿን ፍለጋ የግንብ ፍርስራሽ መሀል መባዘኗ ቀጥሏል፤ ሀዘኗ የያንዳንዱ ወላጅ ሀዘን ሊሆን ይገባዋል። አሌፖ ብቻ ሳትሆን የወደቀችው በጠቅላላው የሶሪያ ነባር ታሪክ እየወደመ ነው፣ ሕዝቧ እያለቀ ነው፣ የተረፈውም በስደት እየተበታተነ ነው። በበኩሌ የሶሪያ ሕዝብ ስቃይና ሀዘን ከሀዘኖቼ ሁሉ ጋር ተቀላቅሎ ይሰማኛል። የአገሪቷ መውደም፣ የታሪኳ መጥፋት አንድ ቀን ብቻ ተሰምቶኝና አስቤው የሚያልፍ ዜና ሳይሆን፤ እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል ሌሊት እየጮኸ ከእንቅልፌ ያባንነኛል።

ከአምስት አመት በፊት ሆይ ብሎ የተነሳው ሕዝባዊ አመጽ ትዝ ይለኛል - **ለነጻነት፣ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲ፣ ለለውጥ የተነሳ እንቅስቃሴ!** ዜናው በመገናኛ ብዙሃን ዘንድ የሠርግና ምላሽ ፍንድቅያ ፈጥሮ ነበር። በድህረ-ገጾች አጠቃቀም የላቁ የትግል ቀስቃሾችና እንዲሁም የተቃዋሚ ኃይል መሪዎች የሆኑ ሁሉ በኩራት ወጥተው ስለድል መቃረብ የሚናገሩበት መቅጽበት ነበር። ብሎም በአለም ዙሪያ በጨቋኝ ሥርዐት ስር የሚማቅቁ ሁሉ ሕዝቦችን የሚቀሰቅስ ስሜት ነበር ያ ወቅት የፈጠረው። ታዲያ ዛሬ ከአምስት አመት በኋላ ያ ሁሉ የት ገባ? የት ደረሰ? ሶሪያ እንዴት እዚህ አስከፊ ጥፋት ውስጥ ልትወድቅ ቻለች? እንዴት 'ከድጡ ወደ ማጡ' ልትገባ ቻለች? የመአከላዊ መንግሥቱን የጭቆና ስርዐት ሊታገልና ሊለውጥ የተነሳ ሕዝብ እንዴት በአክራሪዎች ሊጠለፍና ወደ እርስ-በርስ እልቂት ሊሸጋገር ቻለ? ለዲሞክራሲና ለፍትህ የተነሳ ንቅናቄ እንዴት ከታሪክ በወረሳቸው ቅራኔዎች ላይ በመመሥረት አንደኛው ሌላኛውን የመበቀልና የማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ሊሰማራ ቻለ? የሶሪያ ሕዝብ ለምን ከአፍጋኒስታን፣ ከሶማሊያ፣ ከኢራቅ ሕዝቦች ላይማር ቻለ? *የሶሪያ ጠላቶች እነማን ናቸው? ጠላቶች ካሏትስ በመውደሟ የሚያገኙት ጥቅም ምንድን ነው?*

ከታሪክ ተምሮ ራሱን ሕዝቡንና አገሩን ከጥፋት ለማዳንና ብሎም አዲስ ታሪክ ለመሥራት የሚፈልግ ሁሉ ሊመለከታቸው የሚገባ ሌሎችም ተጨማሪ ተመክሮዎች አሉ። እኛ አፍሪካዊያን ልንዘነጋው የማይገባን ታሪክ አለ- የጥቁር ሕዝብ ልጆች፣ እናቶች፣ አባቶች፣ እህቶችና ወንድሞች ከአህጉራችን ከአፍሪካ እየታደኑና እየታፈኑ፤ በግር-ብረትና በሰንሰለት ታስረው እየተጫኑ ውቅያኖስ ተሻግረው በባርነት እንዲሸጡ ዋና እገዛ ያደረገው በመካከላቸው የነበረው በጎሳ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ግጭት እንደነበረ የታሪክ መዝገቦች የሚያሳዩትን ነው። በዚያ ክፍለ-ዘመን (14ኛው መቶ አካባቢ) በአፍሪካ ውስጥ ተንሰራርቶ የነበረው በጎሰኛ መሪዎች ይካሄድ የነበረው ፖለቲካ፤ የጥሬ ሃብትና የሰው ጉልበት ፍለጋ አለምን ያስሱ ለነበሩት የነጭ ተስፋፊዎች አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸው ነበር። አንደኛውን የጎሳ ንጉሥ በወዳጅነትና በአማካሪነት በመቅረብ፤ ጠመንጃና ጥይት በመለገስም ሆነ በመሸጥና እንዲሁም በተኩስ በማሰልጠን፤ በሌላው ጎሳ ላይ ጊዜያዊ ድል እንዲጎናጸፍ ያደርጉት ነበር። ከዚህ ሴራቸው በስተጀርባ ደግሞ የተሸናፊውን ጎሳ ልጆች እያፈኑ ሲወስዱ 'የተወዳጁት' ንጉሥ እንዳላየ ይሆን ነበር፣ አንዳንዴም ያግዛቸውነበር። የወዳጅ ተብየው አይቀሬ ተራ ሲደርስና የራሱ ጎሳ ልጆች እየተጠለፉ ለሽያጭ ሲላኩ ደግሞ፤ 'ብድር በምድር' በማለት መጀመሪያ የተጠቃው ጎሳ በተራው የተመልካችነቱን ቦታ ይወስድ ነበር። በዚህ መልክ የተከሰተው ሁኔታ ነባር ቅራኔዎችን በማካረርና ግጭቶችን በማባባስ ሕዝቡን በሁሉም አቅጣጫ በማዳካም ለሽያጭና ለልዋጭ እንዲቀርብ አድርጎታል። ከዚያ ቀጥሎ ለተስፋፋው የአውሮፓዊያን ወረራና የቅኝ-አገዛዝ መንሰራራትም መሠረት ሊሆን ችሏል።

### ዋናው ተጠያቂ መንግሥት ወይም ገዥ ቡድን ነው

ሲጠቃለል፤ በጎሳ ላይ የተመሠረቱና የተካረሩ ውስጣዊ የሕዝብ ቅራኔዎች እንደምሳሌ ላነሳሁት የዛሬው የሶሪያ ውድቀትም ሆነ ለአፍሪካ የ400 አመት የባርነትና የቅኝ-አገዛዝ ሥርአት በግብር ላይ መዋል ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ነገር ግን ለቅራኔዎች ባስከፊ

መልክ መካረርና ሕዝብንና አገርን፣ ብሎም ክፍለ-አህጉርን ለጥቃትና ለጥፋት የመዳረግ **ዋና ተጠያቂዎች** የፖለቲካ አገዛዙን ወይም የኀሳ አመራሩን የጨበጡት ቡድኖች መሆናቸው አያጠራጥርም። ተጠያቂነታቸውን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤

1. በሕዝብ መካከል መከፋፈልን የሚፈጥረው ራሱ የገዥዎች **ጨቋኝ አገዛዝ/አስተዳደር** ነው። ይሄም ደግሞ ሊወገድ የማይችል ከራሱ ከሥልጣን-አመጣጡ ጋር የተዋሃደ ባህሪ ነው።

   ዲሞክራሲያዊ የመንግሥት ስርዐትና የሕግ የበላይነት ያልተረጋገጠባቸው ኅብረተሰቦች ሁሉ ውስጥ፤ ገዥዎች ሥልጣን የሚጨብጡት 1. በጥቅም-አጋሮች እየታገዙ በጉልበት ራሳቸውን በመሾም፣ 2. ከዘር በመውረስ፣ 3. እግዚአብሔር የመረጠን ነን በማለት እንደሆነ የታወቀ ነው። በሶስቱም አይነት መንገድ የሚመጡ ገዥዎች ሰፊውን ሕዝብ የሚፈልጉት ለአገልጋይነት እንጅ ሊያገለግሉት፤ ሊጠቀሙበት እንጅ ሊጠቅሙት አይደለም። በእርግጥ አንዱ አምባገነን መሪ ከሌላው በባህሪ ሊለይ ይችላል፤ በአስተዳደር ስልቱና በመዋቅሩም እንደዚሁ። የአስተዳደር ፍልስፍናው ወይም ርዮተ-አለሙ ግን ሰባዊ ክብርናንና ነጻነትን መአከላዊ እስካላደረገ ድረስ ከጭቆና ሊቆጠብ አይችልም።

   አምባገነን ስርዐቶች አላማቸውን ከግብ ለማድረስ በማስፈራራት፣ በማስገደድ፣ አወናባጅ ፕሮፓጋንዳን በመጠቀም ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ከማጋጨት ወደኋላ አይሉም። ለአጥፊ ክፍፍል ሊዳርጉት እንደሚችሉ ቢያወቁም ኃላፊነት ግን አይወስዱም። አመራራቸው በግልና በቡድን ጥቅም ላይ የተመሠረተ፣ ብልህነትና አርቆ-አሳቢነት የሌለው፣ ጦረኛና ትምክህተኛ ነው። የዚህ አይነቶቹ ገዥዎች ሥልጣናቸው ጊዜያዊ እንደሆነ የብዙ መንግሥታት ታሪክ በአለም ዙሪያ ይመሰክራል፤ ጊዜያዊነቱ ግን በእርግጥ አንጻራዊ ነው። ብዙዎቹ ሕዝብንና አገርን ለዘመናት ለማዳከም የሚበቃ ረጅም የሥልጣን እድሜ ነው የሚኖሩት። የመላው አፍሪካ ታሪክ ይመሰክራል።

2. ጨቋኞች ሲውድቁም በስርዐታቸው ሕዝብ ከአዲስ ጭቆና ራሱን መከላከል እንዳይችል አኮላሽተው ነው የሚወድቁት።

   ለብዙ ዘመናት በአምባገነናዊ ስርዐቶች ጭቆና ታፍኖ የኖረ ሕዝብ በቃኝ ብሎ ለአመጽ ሲነሳ አባርነት ከሚያሳዩት ጋር ሆኖ ጨቋኞችን መፈንቀል እንጅ ትኩረቱ፤ የተተኪዎችን ማንነት የመመዘኛ አቅምና ፋታ የለውም። በዚህ የተነሳም ትግሉ ተጠልፎበት ወደ አዲስ ጭቆና ሊሸጋገር እንደሚችል ብዙ ተመክሮዎች ያሳያሉ ። የሃሳብ ነጻነት የሌለበት ስርዐት ውስጥ ታፍኖ የሚኖር ሕዝብ የተለያዩ ፖለቲካ አስተሳሰቦችን በግልጽ ሰምቶ የመተቸት፣ የማወዳደር፣ የመሞከር ወይም የመፈተን ልምድን የሚያገኝበት ሁኔታ አይኖረውምና ለድጋሚ አምባገነናዊ ስርዐት የተጋለጠ ይሆናል። ሀብቱን፣ ንብረቱን፣ ጉልበቱን ለሚፈልጉ የውጭ ኃይሎችም ቀላል መስዋዕት ይሆናል።

### የተቃዋሚ ድርጅቶች ኃላፊነት

ሁልጊዜ ዋና ተጠያቂ መአከለኛ ስልጣን የጨበጠው ኃይል ይሁን እንጅ፤ የሕዝብን የለውጥ እንቅስቃሴ እንመራለን ብለው የሚነሱ ድርጅቶችም ከኃላፊነት ነጻ አይደሉም። የሕዝብን እንቅስቃሴ ወደ ፍሬያማ ግብ ለመምራት፤ **ጨቋኝ ስርዐትን በመለወጥና መሪዎችን በማስወገድ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ጠንቅቆ መገንዘብን ይጠይቃል**፤ ይህ ደግሞ መሪ ድርጅቶች ፍልስፍናቸውን፣ ራዕያቸውንና መዋቅራቸውን እንዲመረመሩ ግዴታ ይጥልባቸዋል። ለውጥ ማምጣት ማለት መጭውን ጊዜ መቅረጽ፣ ለልጆቻችንና ለትውልዳቸው ካለፈውም ሆነ ከዛሬው የተሻለ መሠረት መጣል ማለት ነው፣ ይህ ደግም ያለፈውን ከመተቸትም ሆነ ያለውን ከመዋጋት የከበደ ኃላፊነት ነውና ከትምክህተኝነትና ከጀብደኝነት ስሜት ነጻ የሆነ ብልህ፣ ትሁትና አርቆ አሳቢ አመራርን ይጠይቃል።

ድርጅቶች ውስጣቸውን ለመመርመርና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣት ብቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመገመት እንዲችሉ መመለስ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መሀል ጥቂቶቹን እንደምሳሌነት ከታች እሰነዝራለሁ፤

- ድርጅቱ የግለሰብን **ሰባዊ ክብርናን** ለማረጋገጥና ለማስከበር ምን ያህል የጠና እምነትና ዝግጅት አለው?

- **ለሕግ የበላይነት** ድርጅቱና መሪዎቹ ተገዥ እንዲሆኑ የሚያረጋግጥ (ተግባራዊ የሚያደርግ) ቁራጥ ዝግጅት አለው ወይ?
- ማንኛውም ግለሰብ በጎሳ፣ በዘር፣ በሚከተለው ሃይማኖት ወይም እምነት፣ በቆዳው ቀለምና በመሳሰሉት ባህሪያት እንዲሁም ሰባዊ ነጻነቱን በመመርኮዝ ባደረጋቸው የግል የአኗኗር ምርጫዎች የተነሳ እንዳይጨቆን ድርጅቱ ምን አይነት የጠና እምነትና ዝግጅት አለው?
- ድርጅቱ የራሱን ራዕይ ከሌሎች ድርጅቶች ራዕይ ምን ያህል አስበልጦ ያያል?
- ድርጅቱ የአባሎቹንም ሆነ የሌሎች ድርጅቶችን ትችት፣ ሂስና ሃሳብ **በነጻና በዴሞክራሲያዊ መንገድ** ለመስማትና ራሱን ለመለወጥ ወይም አቅጣጫውን ለማስተካከል ምን ያህል ቁራጥና ዝግጁ ነው?
- ድርጅቱ የሚዘጋጀው ራሱን ከሌሎች ድርጅቶች መሀል ለሕዝብ ምርጫ ለማቅረብ ነው ወይስ ጨቋኞች ሲወገዱ የመሪነት ቦታውን በቀጥታ ለመውሰድ ነው?

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ዋዜማና የጥቁር ሕዝብ ትንሳኤ

’ዲሞክራሲ፣ ፍትህ፣እኩልነት፣ሰብአዊ ክብርናና ነጻነት፣ የሕግ የበላይነት’ በሚሉት መፈክሮች ሥር በኢትዮጵያ የተካሄደው የፖለቲካ ትግልና እንቅስቃሴ 40 አመታት አልፈውታል። ይሄን በተመለከተ በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር 1974 የፈነዳው ’የየካቲት አብዮት’ በይዘቱም ሆነ በቅንብሩ እንዲሁም በተከፈለበት ዋጋ ሊዘነጋ የማይችል ታሪካዊ ቦታ አለው። በሕብረ ብሔራዊ ድርጅቶችም ሆነ በብሔር ድርጅቶች ሥር ተሰልፈው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሕይወታቸውን ለሕዝባቸው፣ ለወገኖቻቸውና ለአገራቸው ፍቅር ሲሉ ሰውተዋል። በዚህ ብርቅ ታሪካችን ላይ ብዙ የተለያዩ ስሜቶች እንዳሉ አውቃለሁ፤ ቢኖሩም ማስገረም የለበትም። ታሪክ፣ የቅርቡም የሩቁም፤ ሁልጊዜ አወዛጋቢ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፤ አካላቸው ላይ ጠባሳ መንፈሳቸው ውስጥ የማይደርቅ ቁስል ይዘው የሚኗዙ በሕይወት የሚኖሩ ብዙ ወገኖች ስላሉ ነው። እነሱንና ትናንትናም ዛሬም በአዲስ ጥይት የሚወድቁትን ወገኖቻችንን የሚያስተሳስራቸው አንድ ነገር ነው - ለውጥ ማምጣት!

*ሕዝብ ከትውልድ ትውልድ እየደማ፣ ለድል ቀን ሳይደርስ በድል ዋዜማ እየወደቀ እንዳይቀር፣ የዛሬው ዋዜማ የመጨረሻው እንዲሆን የማድረግ አደራ አለብን፤ ችሎታውም በእጃችን ነው። አደራችን የጠቅላላው የጥቁር ሕዝብ አደራ ነው።*

የጥቁር ሕዝብ አደራ ነው ስል ምን ማለቴ እንደሆነ እንድትረዱኝ ሃሳቤን ባጭሩ ከታች እገልጻለሁ፤

> ኤኮኖሚን በተመለከተ ምዕርባዊያንም ሆኑ ቻይናና መሰሎቿ የምግብ ማምረቻ መሬት፣ የጥሬ ሃብትም ሆነ የገበያ ቦታ በሰፊውና በግልጽ በመሻማት ላይ ከተሰማሩ ቆይተዋል። ለዚህ ሽሚያ ዋና ትኩረት የሚደረገው በመላው አፍሪካ ላይ ነው። ይሄም የሚካሄደው አንደኛውን ወገን ብቻ በሚጠቅሙና ፈጽሞ እኩልነትን ባልተመረኮዙ ስምምነቶች ላይ በተመሠረቱ ውሎች አማካኝነት ነው። ለምሳሌ ያህል ይሄ ሂደት ባገራችን በሰፊው የተከሰተና መፈናቀልንና የርስበርስ ግጭቶችን እያስከተለ ያለ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከእኛ አገር አንስቶ በመላው አፍሪካ ውስጥ ያንሰራሩት የገዥ ስርዐቶች የሚካሄደው ቅርምጫ በአገሮችና በሕዝቦችም ላይ ሆነ በመላው አህጉር ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት የሚገነዘቡ አይደሉም። (የብዝበዛ እንጅ የንግድ ተቃዋሚ አለመሆኔን አሳስባለሁ።)
>
> በአለም ውስጥ የሕዝብ ብዛት እየጨመረ በሄደበት፣ የተዛባ የሀብትና የእውቀት ስርጭት ጎልቶ በሚታይበት፣ የወታደራዊ ኃይል በጥቂት አገሮች እጅ በገነነበትና አዳዲስ አክራሪና የነጭ የበላይነትን የሚያንጸባርቁ መሪዎች ብቅ ብቅ በሚሉበት ወቅት በአፍሪካና በጥቁር ሕዝብ ላይ ከምንጊዜው የበለጠ አደጋ እያንዣበበ መሆኑን ያመለክታል። ምንም እንኳን አደጋው የአለም በሙሉ ቢሆንም።
>
> ሰባዊ ክብርናንና ደህንነትን በሚመለከት፤ ጥቁር ሰው ዛሬም በያለበት መጨቆኑ አልቀረም። በይዘቱ በስፋትና በጥልቀቱ ትንሽ ይለያይ እንጅ ዛሬም በቆዳው ቀለም ላይ በተመሠረተ ጭቆና ይጠቃል። እንደስደተኛም ሆነ እንደዜጋ በእኩልነት የማይታይበት ጊዜ ብዙ ነው፣ በሕግ ፊት ሁልጊዜ እኩል አይሆንም፣ በፍርደ ገምድሎች የመጠቃት አደጋው የበዛ ነው። በዚህም የተነሳ ሁልጊዜ ፈተና ላይ ይወድቃል። ሆኖም የጥቁር ልጆች በመላው አለም፣ በያሉበት ኅብረተሰብ ያሚያስከብራቸውን ሥራ እየሰሩና አኩሪ ተግባር እየፈጸሙ እንደሚኖሩ አብሮ መነገር አለበት። ከሌሎቹ ሕዝቦችም ጋር

ተደባልቀውና ተዋልደው ይኖራሉ። ጥቁሩ እንደግለሰብነቱ እጣ ፈንታው የተለያየ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ሆኖም ግን እንደጥቁር ሕዝብ አዲስ ታሪክ መጻፍ ይገባናል። ከቀሩት ያለም ሕዝቦች ጋር በመተባበር እኩልነት፣ ሰባዊነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ለሁሉም የተረጋገጠበትና ሰላም የሰፈነበት አለም ለመፍጠር አስተዋጾ ለማድረግ መብቃት አለብን። ለዚህ የምንበቃው መጀመሪያ ራሳችንን ስናውቅና ስናከብር ነው። መጀመሪያ ከጨቋኝ ስርዐቶች ስንላቀቅና ተመልስነም ምንጊዜም በጨቋኞች እጅ የማንወድቅበትን መሠረት ስንተክል ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የተነቃነቀው ትግል አቅጣጫውን ወደዚህ ቢያደርግ ግብ ሊመታ ይችላል የሚል እምነት አለኝ። ትግሉ የጋራ ጥቃቶችን መገንዘብ አለበት፣ ያጭርና የረጅም ጊዜ ጥቅሞችን ለይቶ ማየት አለበት። ለአያት ለቅድመ-አያቶቹ ታሪክ ትውልዱን መስዋእት ማድረግ አያስፈልገውም፣ ለውርሱ ተገቢውን ቦታ ሰጥቶ አዲስ የራሱ ታሪክን ለመጻፍ መድፈር አለበት። ሰፊ ሃገርና ድንበርም ሆነ በርካታ ሕዝብ ኃይል ነው፤ ህብራዊነትና ብዙኃንነት የእውቀትና የሃብት ምንጭ ነው።

ከተለያየ እይታ በመነሳት ማንም ይጻፈው ማንም ሳይበላለጥና ሳይተናነስ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለሰባዊ መብት የታገሉት ወገኖቻችንን አደራ የመወጣት እድሉ ገና ጨርሶ አላመለጠንም። ተከራክረንና ተደራድረን፤ ግን ተባብረን ነጻነቱ የተከበረለት፣ እኩልነቱና ሰባዊ መብቱ የተረጋገጠለት፣ ተደጋግፎና ተረዳድቶ ጭቆና፣ ድህነትና ረሀብ የጣሉበትን ውርደት የሚላቀቅ፣ በኅብረትና በታደሰ አንድነት የሰላምና የጸጥታ ዋስትና ፈጥሮ መኖር የሚችል ሕዝብ እንዲኖረን ካሰብን ከራሳችን በቀር የሚያግደን ማንም የለም።

*ወገኖቻችን ከድል ዋዜማ ወደ ድል ተሸጋግረው ለመላው የጥቁር ሕዝብ ትንሳኤ ምሳሌነት ሊበቁ እንዲችሉ ለማድረግ የሚያበቃ ፍላጎትም ሆነ ችሎታ አለን ብዬ አምናለሁ!*

የሺወርቅ ወንድሜነህ